# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

# የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን

## የግንባታ እና የእርሻ መሣሪያዎች ኦፕሬተር ብቃት

## ማረጋገጫ ፈቃድ አሰራር መመሪያ 684/2013

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ሚያዝያ 2010 ዓ.ም

# <u>የግንባታ እና የእርሻ መሳሪያዎች ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠራር መመሪያ 23/2010</u>

## <u>መግቢያ</u>

የትራንስፖርት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7(2)(በ) ባለሞተር ተሽከርካሪ መንዳት ለሚያስተምሩ ሰዎችና ማሰልጠኛ ተቋማት የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ማውጣትና ተግበራዊነቱን መከታተል እና እንዲሁም በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 8 የማሰልጠኛ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኛት ማሟለት ያለባቸዉ ሀገር አቀፍ መስፈርቶችን በመመሪያ የመወሰን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የግንባታ እና የግብርና ስራዎች ብቃት ባላቸው ኦፐሬተሮች ለማገዝ ኦፐሬተሮችን በብዛትና በጥራት ማፍራት ይቻል ዘንድ መስፈርቱን በመሟላት የግንባታ እና የእርሻ መሳሪያዎች ኦፐሬተሮች ስልጠና ለመስጠት ጥያቄ የሚያቀርቡትን ማንኛውም የመንግስት አካላትን፣ ድርጅቶች እና የግል ባለሀብቶችን በመስኩ ተሳታፊ ማድረግ የሚያስችል የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

የግንባታ እና የእርሻ መሳሪያዎች ኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ  አሰራር መመሪያ 684/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ2፤ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 አንቀጽ/2 የተዘረዘሩት ቃላትና እና ሐረጎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላት ወይም ሐረጎች የሚከተሉት ትርጓሜ ይኖራቸዋል

1. "የሰልጣኝ መታወቂያ" ማለት ትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ማሰልጠኛ ተቋሙ ለሠልጣኙ አዘጋጅቶ የሚሰጠው መታወቂያ ነው፡፡

2. "የአሰልጣኝ መጣወቂያ" ማለት ትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና የተሰጠው አካል አዘጋጅቶ ለአሰልጣኙ የሚሰጥ መታወቂያ ነው፡፡

3. "ተቆጣጣሪ" ማለት ከምዝገባ እስከ ብቃት ማረጋገጫ ሠርተፍኬት አሰጣጥ ያለውን ሂደት የሚቆጣጠር የትራንስፖርት ባለስልጣን ሠራተኛወይም ባለስልጣኑ የሚወክለው አካል ነው፡፡

4. "ፈቃድ ሰጪ" ማለት ብቃቱ የተረጋገጠለት የኮንስትራክሽን ማሽነሪ እና የእርሻ መሣሪያዎች ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጥ በባለስልጣኑ የእዉቅና ሠርተፍኬት የተሰጠዉ ማንኛውም አግባብነት ያለው የመንግስት አካል ወይም ትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡

5. "መሳሪያ (ማሽነሪ)" ማለት ለግንባታ፣ ለግብርና፣ ለዕቃ ማንሻ ወይም ለቁፋሮ ስራ አገልግሎት የሚውል የሰውን ጉልበት በማገዝስራን የሚያፋጥን ባለጎማ ወይም ባለሰንሰለት እግር ያለው ማንኛውም በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ መሳሪያ ነው

6. "ማሠልጠኛ ተቋም" ማለት ህጋዊ ፈቃድ ያለውና ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሠረት የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያዎች ኦፕሬተሮችን የንድፈ ሃሳብና የተግባርስልጠና በመስጠት ለውጤት የሚያበቃ ድርጅት ነው፡፡

7. "የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት" ማለት የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ የኦፕሬተርነትን ስልጠና በበቂ ሁኔታ ላጠናቀቁ አካላት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

8. "የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከል" ማለት ትራንስፖርት ባለሥልጣን ከቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ጋር በሚኖረው የጋራ ስምምነት መሰረት ስልጠናቸውን ላጠናቀቁ

የኮንስትራክሽን ማሽነሪ እና የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲሰጥ እውቅና የተሰጠው ማዕከል ነው፡፡

9. "ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ" ማለት የስምንተኛ ክፍል ፈተና ማለፉን የሚያሳይ አግባብነት ካለው ትምህርት ቢሮ የተሰጠ የት/ት ማስረጃ ነው፡፡

10. "አሥራኛ ክፍል ያጠናቀቀ" ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠዉን የአስራኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና መውሰዱን የሚያሳይ የት/ት ማስረጃ ነዉ.

11. "አዋጅ " ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 ነዉ.

## 3. ዓላማ

"ግልፅ፣ ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው የዕጩ የግንባታ እና የእርሻ መሣሪያዎች ኦፕሬተሮች የምዝገባ፣ የስልጠና፣ የፈተና ስርዓትን በመተግበር ብቃትና ጥራት ያላቸው ኦፕሬተሮችን ማፍራት የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በማናቸዉም የግንባታ ወይም የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተር ስልጠና በሚሰጡ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ የኦፕሬተር ስልጠና በሚከታተሉት ዕጩ ኦፕሬተሮች፣ የኦፕሬተሮችን ብቃት በሚያረጋግጡ እና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በሚሠጡ እንዲሁም የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በያዙት ኦፕሬተሮች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ጌጣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ሁለት

## ስለ ግንባታ ወይም እርሻ መሳሪያዎች ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ

5. **ለግንባታ ወይም ለእርሻ መሣሪያዎች ኦፕሬተር ፈቃድ ስልጠና ዕጩ ሰልጣኞች ስለሚጠየቁ ማስረጃዎች**

1. የጤንነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ፈቃድ ከተሰጠውና በአካባቢዉ ከሚገኝ የመንግሥት ወይም የግል ህክምና ተቋም
2. የታደሰ የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የልደት ሠርተፍኬት ወረቀት
3. የእጩ ኦፕሬተር ሰልጣኝ ዝቅተኛ ዕድሜ 20 ዓመት ሆኖ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ መሆኑን የሚገልፅ
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ከተገለፀዉ የትምህርት ማስረጃ በተጨማሪ አግባብነት ካለው ትምህርት ቢሮ የተሰጠ የ8ኛ ክፍል ሰርተፍኬት የትምህርት ማስረጃ
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰዉን ማቅረብ የማይችሉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከሚሰሩበት መ/ቤት ወይም ትምህርት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ በማቅረብ በመ/ቤቱ ወይም በዩኒቨርሲቲ መታወቂያ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

6. <u>ስለሰልጣኞች ምዝገባ</u>

1. ሰልጣኞች በፖስታ ወይም በኢ-ሜል፣ ወይም በግንባር በመቅረብ በማሠልጠኛ ተቋማት መመዝገብ ይችላሉ
2. ሰልጣኝ ሥልጠና ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ 5 ቀን አስቀድሞ በማሠልጠኛ ተቋማት መመዝገብ አለበት

7. <u>ንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና በተመለከተ</u>

1. የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠናው በተዘጋጀው የስልጠና መስጫ ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት መሆን፤
2. በመረሀ ግብሩ ስልጠና መስጠቱ እንዳተጠበቀ ሆኖ በቀን ዉስጥ ከ4 ሰዓት ያልበለጠ በወርክ ሾፕ የተደገፈ የንድፍ ሀሳብ ስልጠና በስልጠና ማዕከሉ ይሰጣል፤

3. በስልጠና መስጫ ሥርዓተ ትምህርት የተቀመጠው የተግባር ስልጠና ሰዓት እስኪጠናቀቅ ድረስ አንድ ሰልጣኝ በየቀኑ አንድ(1) ሰዓት የተግባር ስልጠና መሰልጠን፤

4. ሰልጣኞች በንድፈ ሀሳብ የቀሰሙትን ዕውቀት በተግባር እንዲያዳብሩ መስፈርቱን ያሟላ እና የማሽን ብዛትን ግምት ዉስጥ ያስገባ በግል ወይም በጋራ ባለቤት የተያዘ የሰርቶ ማሳያ ቦታ መኖር፤

5. ሠልጣኞች በንድፈ ሀሳብ ያገኙትን ሥልጠና በተግባር እንዲያዳብሩ በግል ይዞ፤ በኮንትራት ወይም በኪራይ የተመዘገበ እና ማስረጃው በሚመለከተው የመንግስት አካል የተረጋገጠ ስፋቱ ከ5000 ካ.ሜ ያላነሰ በአንድ ወይም በተለያየ ቦታ መሆን ይችላል፡፡ በተለያየ ቦታ የሚሆን ከሆነ በአንድ ቦታ ሊኖር የሚችል ዝቅተኛ የሰርቶ ማሳያ ቦታ ስፋት ቢያንስ ከ2000 ካ.ሜ ማነስ የለበትም፡፡

6. አጠቃላይ የሁሉም ተቋማት የማሰልጠኛ ማሽነሪ ብዛት አራት እና ከአራት በታች ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 የተጠቀሰዉን መስፈርት ያሟላ የተግባር ስልጠና መስጫ ቦታ በጋራ ሊኖር ይቻላል

7. የሰርቶ ማሳያ ቦታ በኪራይ ወይም በኮንትራት የሚቀርብ ከሆነ የኪራይ ውሉ ወይም የኮንትራት ውሉ የጊዜ ገደብ ቢያንስ አንድ ዓመት እና ከአንድ ዓመት በላይ መሆን

8. የስልጠና (የማስተማሪያ) ቋንቋ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ወይም በአካባቢ (በክልሉ የሥራ ቋንቋ) ሊሆን ይችላል፡፡

9. የንድፈ ሀሳብና የተግባር አሰልጣኞች የማሰልጠኛ ተቋሙ ቋሚ ቅጥር መሆን አለባቸው

10. በአንድ የስልጠና ዙር በአንድ ማሽን መሰልጠን የሚገባው የሰልጣኞች ብዛት ቁጥር ከአሥር(10) መብለጥ የለበትም

11. የማስተማሪያ ክፍሎች እና የቢሮ ሕንፃ በኪራይ የሚቀርብ ከሆነ የኪራይ ውሉ በውልና ማስረጃ የተደገፈ ሆኖ የኪራይ ውሉ ጊዜ ገደብ ከአንድ ዓመት ያላነሰ መሆን አለበት

12. ማንኛውም ሰልጣኝ በተግባር ስልጠና ወቅት የደህንነት መጠበቂያ ልብስ ለብሰው መሰልጠን አለበ

ከማሁን ን/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

8. <u>በየስልጠና ምድቡ እና ማሽን ዓይነት ሊኖር የሚችል የስልጠና ሰዓት</u>

| ተ.ቁ | የማሽን ዓይነት | የስልጠና ጊዜ በሰዓት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የንድፈ ሀሳብ ስልጠና (ሀ) | የተግባር ስልጠና (ለ) | ጠቅላላ የስልጠና ሰዓት (ሀ+ለ) |
| 1 | ሎደር | 47 | 33 | 80 |
| 2 | ባክሁሎደር | 25 | 30 | 55 |
| 3 | ፎርክ ሊፍት | 25 | 33 | 58 |
| 4 | ትራክተር | 23 | 35 | 58 |
| 5 | ሩሎ | 25 | 30 | 55 |
| 6 | ዶዘር | 34 | 44 | 78 |
| 7 | ስክራፐር | 35 | 41 | 76 |
| 8 | ግሬደር | 35 | 48 | 83 |
| 9 | እስካቫተር | 43 | 45 | 89 |
| 10 | ኮምፓይነር | 21 | 40 | 61 |
| 11 | ክሬን | 55 | 45 | 100 |

9. <u>ስለንድፈ ሃሳብ ፈተና አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም ተፈታኝ ወደ ፈተና ጣቢያ ሲመጣ የስልጠና መከታተያ መታወቂያ ካርድ ይዞ ሲቀርብና ማንነቱ ሲረጋገጥ የንድፈ ሃሳብ ፈተና ይወስዳል፡፡
2. ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኞች ስለፈተናው አሰራር በግልፅ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት

3. ተፈታኝ የሚፈተንበትን ቦታ እና ሰዓት በሚማርበት ማሰልጠኛ ተቋም በኩል ከአንድ ቀን በፊት አስቀድሞ ማወቅ አ
4. ተፈታኞች ፈተና ከሚጀምሩበት 15 ደቂቃ ቀደም ብለው በቦታው መገኘት አለባቸው
5. የንድፍ ሀሳብ ፈተና ጥያቄ ብዛት 50 ሆኖ ሁሉም ጥያቄ ምርጫ ይሆናሉ
6. ዝቅተኛ የንድፈ ሀሳብ ፈተና የማለፊያ ነጥብ 74% ነዉ
7. 85% እና ከዚያ በላይ የስልጠና ሰዓት የተከታተለ ሰልጣኝ ብቻ ለፈተና የሚቀመጥ ይሆናል
8. እያንዳንዱ ተፈታኝ ፈተናውን እንደጨረሰ ወዲያውኑ በተፈተነበት ኮምፒዩተር የፈተና ውጤት እንዲያውቅ ይደረጋል፡
9. የፅሁፍ ፈተናዉ በወረቀት የሚሰጥ ከሆነ የተፈታኙ የፅሁፍ ፈተና ውጤት በ7 ቀናት ውስጥ እንዲያውቅ ይደረጋል
10. የምዘና ቋንቋ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ወይም በአካባቢ (በክልሉ የሥራ ቋንቋ) ሊሆን ይችላል፡፡

## 10. ስለተግባር ፈተና አሰጣጥ

1. ማንኛውም ተፈታኝ ወደ ፈተና ጣቢያ ሲመጣ የስልጠና መከታተያ መታወቂያ ካርድ ይዞ ሲቀርብና ማንነቱ ሲረጋገጥ የተግባር ፈተና ይወስዳል፡፡
2. የተግባር ፈተና ዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከል መስፈርት መሰረትነው
3. ፈታኝ ባለሙያ በፈተና ወቅት የራሱን መለያ ባጅ ደረቱ ላይ ማንጠልጠል አለበት
4. የተግባር ፈተናው ይዘት በሥርዓተ ትምህርቱ በተቀመጡ የመመዘኛ መስፈርቶች መሠረት ይሆናል

## 11. ስለብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች

ሰልጣኞች በስርዓተ ትምህርቱ መሠረት ስልጠናቸውን በአግባቡ ማጠናቀቃቸው ሀላፊነት በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ሊሰጣቸው ይችላል

1. በማሰልጠኛ ተቋማት የሚሰጥ ትራንስክሪብት እና ሰርተፍኬት

2. ከሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት
3. በትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ዉክልና በተሰጠዉ አካል በሰለጠኑበት የማሽን ዓይነት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

## 12. መረጃና ሪፖርት ስለመላክ

1. የማሰልጠኛ ተቋማትበሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተመዝነው ብቃታቸው የተረጋገጠ ዝርዝርና ሙሉ መረጃ በየምዘና ዙር ለባለስለጣን መ/ቤቱ ወይም ዉክልና ለተሰጠዉ አካል ሪፖርት ማድረግ
2. ማሰልጠኛ ተቋማት የስልጠና መርሃ ግብር እና የተሟላ የሰልጣኞች መረጃ ስልጠና ከመጀመሩ ከ3 ቀን በፊት ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ዉክልና ለተሰጠዉ አካል ማሳወቅ አለባቸዉ፡፡

## 13. ስለጠፋ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምትክ ወይም ግልባጭ ስለመስጠት

1. የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የጠፋበት ኦፕሬተር በአካል መታወቂያ ይዞ ሲቀርብ፤
2. የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በትክክል መጥፋቱን ከፖሊስ ማስረጃ ሲቀርብ፤
3. የጠፋበት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የዕድሳት ጊዜ ገደብ ያላለፈበት መሆኑ ሲረጋገጥ
4. የጠፋበት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የእድሳት ጊዜ ገደቡ ያላለፈበት ከሆነ የአገልግሎት እና የደብተር ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ነገር ግን የዕድሳት ጊዜ ገደብ ያለፈበት ከሆነ ጊዜ ያለፈበት ውዝፍ ክፍያ ጭምር እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
5. የጠፋበት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የዕድሳት ጊዜ ያለፈበት ከሆነ ኦፕሬተሩ የተግባር ፈተና ወስደው ብቁ ሆኖ ሲገኝ ግልባጭ መንጃ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

6. ፈቃድ ሰጪው አካል የጠፉ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዶችን በመረጃ መረብ ወይም በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ዋጋ እንደሌላቸው ማሳወቅ አለበት

7. በአንድ ዓመት ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የጠፋበት መሆኑን በመግለፅ ምትክ እንዲሰጠው ጥያቄ የሚያቀርብ ኦፕሬተር ግልባጭ ማግኘት የሚችለው የምትክ መደበኛ ክፍያ ሶስት እጥፍ እንዲከፍል ይዳረጋል

8. በአንድ ዓመት ከሶስት ጊዜ በላይ የጣለ ኦፕሬተር በጣለዉ ቁጥር በሶስተኛ የምትክ የከፈለዉ ክፍያ ላይ አንዳንድ እጠፍ እየጨመረ እንዲከፍል ይዳረጋል

## 14. <u>የኦፕሬትር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት</u>

1. የማንኛዉም ምድብ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለአራት ዓመት ይሆናል

2. ማንኛዉም የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ኦፕሬተር የዕድሳት አገልግሎት የሚሰጠው የጤንነት ምርመራ ውጤት ሲያቀርብና ተገቢዉን ክፍያ ሲፈፅም በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ለአራት ዓመት ይታደሳል

3. የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆየዉ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ ለ4ዓመት ሆኖ ጊዜ አልፎበት በአንድ(1) ዓመት ዉስጥ ቀርቦ ያላሳደሰ ብቃቱ በፈተና ተረጋግጦ እንዲታዳስለት ይደረጋል

4. የእድሳት ጊዜ ገደብ ያለፈበት ኦፕሬተር ደረጃውን የሚመጥን ማሽነሪ በግሉ ወይም ከማሰልጠኛ ተቋም ወይም ከሚሰራበት መ/ቤት በማቅረብ የተግባር ፈተና ተፈትኖ ሲያልፍ የዕድሳት አገልግሎት ያገኛል

ከማሁን ኃ/ማርያም
ም/ ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

## ክፍል ሶስት

## የተለየዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 15. የትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

የትራንስፖርት ባለሥልጣን በአዋጅ 468/1997፣ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 እና በሌሎች ህጎች የተሠጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-


1. ዉክልና ለተሰጠዉ አካል እና ለማሰልጠኛ ተቋማት በአዋጁ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የአሰራር መመሪያዎችን እና መስፈርቶችን ያወጣል፣ ያሰራጫል፣ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል
2. ማሰልጠኛ ተቋማት በመስፈርቱ መሰረት መደራጀታቸዉን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል እንዲሁም ከመስፈርት በታች በሆኑት ላይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል
3. ፈቃድ የተሰጣቸዉ ማሰልጠኛ ተቋማትን የመደጋፍ፣ የመከታተል እና የመቆጣጠር ተግባራትን ያከናዉናል።
4. የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል።
5. የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ የኦፕሬተሮች አሰልጣኞች ስልጠና ለሚሰጡ የመንግስት አካላት ዉክልና ይሰጣል ወይም በራሱ ሊያሰለጥን ይችላል
6. የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተሮች ብቃት ማረጋገጥ በተመለከተ እንዳስፈላጊነቱ መንግስት ተቋማት ውክልና መስጠት ይቻላል
7. ፈተናን በተመለከተ ትራንስፖርት ባለስልጣን እንደ አስፈላጊነቱ ወቅቱን የጠበቀ መስፈርት ሊያወጣ ይችላል
8. ከዋናው (ከኦርጅናል) ጋር የተገናዘበ እና የተረጋገጠ የሠልጣኞች መረጃ ፎቶ ኮፒዉን መያዝ

## 16. በባለስልጣኑ ዉክልና የተሰጠዉ አካል ተግባርና ኃላፊነት

1. ባለስልጣኑ ባዘጋጀው መስፈርት መሰረት መደራጀት
2. የማሰልጠኛ ተቋማት እና የራሱን አፈፃፀም ለትራንስፖርት ባለስልጣን በየሶስት ወሩ ሪፖርት ማድረግ
3. መስፈርት አሟልተው የተገኙ እጩ ኦፕሬተሮችን ብቻ አጣርቶ መፈተን ወይም ማስፈተን
4. ፈታኝ ባለሙያዎችን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ማሟላት
5. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው ይዘት፣ ቅርፅና ጥራት መሰረት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት
6. በስልጠና እና በፈተና ላይ የሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮችን መከታተልና ማስወገድ
7. ስልጠና አጠናቆ ከሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት ሰርተፍኬት ለተሰጣቸው የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተሮች ከስልጠና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት
8. ከዋናው (ከኦርጅናል) ጋር የተገናዘበ እና የተረጋገጠ የሠልጣኞች መረጃ ፎቶ ኮፒዉን መያዝ

## 17. የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት መደራጀት
2. በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ዕጩ ኦፕሬተሮችን መቀበል እና ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና መስጠት፤



3. የተቀበላቸውን የሠልጣኞች ስም ዝርዝር ከተሟላ መረጃ ጋር፣ የስልጠና ማሽነሪዎች ብዛት ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማሳወቅ

4. የስልጠና መርሃግብር አዘጋጅቶ ስልጠና ከመጀመሩ ከ3 ቀን በፊት በማሳወቅና ከትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ሲፈቅድለት ብቻ ስልጠናዉን መጀመር፡፡

5. ስልጠናቸውን ያጠናቀቁ እና ለፈተና ብቁ የሆኑ የሠልጣኞችን ስም ዝርዝር በወቅቱ ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማስተላለፍ፡፡

6. በየስልጠናዉ ዙር አፈፃፀማቸውን ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

7. በአፈፃፀም ወቅት ያጋጠማቸውን ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማሳወቅ

8. በተዘጋጀው የስልጠና መርሀ ግብር መሰረት ለየምድቡ የተቀመጠ የስልጠና ሰዓት ሙሉ በሙሉ ማሰልጠን

1. የሠልጣኞች መረጃ ፎቶ ኮፒዉ ከዋናው (ከኦርጅናል)ጋር አገናዝቦና አረጋግጦ ፎቶ ኮፒው ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማስተላለፍ

2. ሰልጣኞች የሚያቀርቡትን የትምህርት፣ የጤና፣ መታወቂያ እና የሌሎች ማስረጃዎች ትክክለኛነት ማረጋገጥ

18. <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ተግባርና ኃላፊነት</u>

በቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ በህግ የተሠጣቸው ኃላፊነት እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ከትራንስፖርት ባለስልጣን ጋር በሚኖረው ስምምነት መሠረት፡-

3. ስልጠናቸውን አጠናቀው ከትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል የሚላኩ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሣሪያ እጩ ኦፕሬተሮችን መቀበል፤

4. ስርዓተ ትምህርቱ ላይ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት የዕጩ ኦፕሬተሮች ብቃት ማረጋገጥ

5. ብቃታቸው እንዲረጋገጥ የተላለፉ እና ብቃታቸው የተረጋገጠ ኦፕሬተሮች ስም ዝርዝር ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ማስተላለፍ

6. በምዘና ወቅት ያጋጠማቸውን የክህሎት ክፍተቶች መዝጋት የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና ለተሰጠው አካልማሳወቅ

7. ተመዝነዉ ላለፉ ሰልጣኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /C.O.C. Certificate/ አዘጋጅቶ መስጠት

8. የምዘና ጥራትን ሊያጓድሉ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮች በመፈተሽ የመፍትሄ እርምጃዎች መውሰድ፣ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ

19. <u>የሰልጣኝ መብትና ግዴታ</u>

1. ሰልጣኞች በምዝገባ ወቅት ትክክለኛና ህጋዊ የትምህርት ማስረጃ፣ የቀበሌ መታወቂያና የህክምና ሰርተፊኬት ማቅረብ፤

2. በስልጠና ፕሮግራም መሰረት በንድፍ ሃሳብና በተግባር ስልጠና ወቅት በሰዓቱ በቦታው መገኘት እና መሰልጠን

3. የንድፍ ሃሳብና የተግባር ስልጠና ሰዓት ሳይሸራረፍ ሙሉውን ሰዓት መሰልጠን፤

4. በስልጠና ቦታና ሰዓት ሰልጣኙ የተቋሙን የምዝገባ ቁጥር የያዘ የስልጠና መታወቂያ (Learners permit) (ባጅ) ማንጠልጠል፤

5. የማሰልጠኛ ተቋም እና የትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ውክልና የተሰጠው አካል የስነ ስርዓት ደንቦች ማክበር፤

6. ስልጠና የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት የስልጠና መርሀ ግብር አስቀድሞ ማወቅ

7. በስልጠና መርሀ ግብር መሰረት ሙሉ የንድፉ ሀሳብና የተግባር ስልጠና መውሰድ

ኢማሁን ኃ/ማርያም
ም/ ዳይሬክተር

## ክፍል አራት

## 20. የግንባታ ወይም የእርሻ መሣሪያ ኦፕሬተር ማሠልጠኛ ተቋማት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚያስፈልጉ መስፈርት (Standards)

### 1. የቢሮ አደረጃጀት

ሀ. የተቋሙ ዳይሬክተር ቢሮ፤

ለ. የምዝገባና ገንዘብ ተቀባይ ሠራተኛ ቢሮ፤

ሐ. የንድፈ ሃሳብና የተግባር አሰልጣኞች ቢሮ፤

መ. ለሰልጣኝና ለባለጉዳዩ እንዲሁም ለሠራተኞቹ በቂና ምቾት ያለው ቢሮዎች፣ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች እና

ሠ. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችና የመገልገያ መሣሪያዎች መኖር አለበት

### 2. የማስተማሪያ ክፍሎች

ሀ. ስፋቱ 5 ሜትር በ6 ሜትር (30 ካ.ሜ) የሆነ ነጠላ ዴስክ፣ ጠረጴዛዎች፣ ነጭ ወይም ጥቁር ሠሌዳ ያለው የማስተማሪያ ክፍሎች፤

ለ. በቂ ብርሃንና ተስማሚ አየር የሚያስገቡ መስኮቶች ያሉትና ጣሪያቸውቢያንስ 2.5ሜ ከፍ ብሎ የተሰሩ ክፍሎች፤

ሐ. በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት የተዘጋጀ በቂ የማስተማሪያ መጽሃፍ፣ ህጎች፣ የማሽነሪዎች ማንዋል፣ የማጣቀሻ መጽሃፎች እንዲሁም የሰልጣኞችን እና የአሰልጣኞችን የዕውቀት አድማስ የሚያሰፉ መጽሄት፣ ጋዜጣዎች ያለውና ቢያንስ በአንድ ጊዜ 15 ሰው የሚያስተናግድ ቤተ መጽሃፍት፤

መ. እያንዳንዱ ሰልጣኝ በኮምፒዩተር ላይ መሰልጠን በሚችል መልኩ በሚገባ የተደራጀ የጽሁፍ ፈተና ጥያቄ የተጫነበት ቢያንስ 10 ኮምፒዩተር ያለው የኮምፒውተር ማለማመጃ ክፍል፤

ሠ. የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ፤

ረ. የማስተማርና የመማር ሂደቱን የማያደናቅፍ ጫጫታ የሌለው አካባቢ መሆን፤

ሸ. የመፀዳጃ ክፍል ለወንድና ለሴት ለየብቻ፤

## 3. የወርክ ሾፕ አደረጃጀት

የወርክ ሾፕ ስፋት ቢያንስ 50 ካሬ ሜትር ሆኖ ተገጣጥሞ እና ተበታትነዉ የሚታይ

ሀ. የሚሰራ የማሽን ሞተር፤

ለ. የተሟላ የማሽን ኃይል አስተላላፊ ክፍሎች፤

ሐ. የተሟላ የማሽን ነዳጅ አስተላላፊ ክፍሎች፤

መ. የተሟላ የማሽን የሃይድሮሊክ ሲስተም ክፍሎች፤

ሠ. የተሟላ የኤሌክትሪክ ክፍሎች እንዲሁም ለስልጠና አስፋላጊ የሆኑ የተለያዩ የማሽነሪ ክፍሎች

## 4. የተግባር ስልጠና መስጫ መሳሪዎችን በተመለከተ

ሀ. አዲስ ወይም ቅርንጫፍ የግንባታ ወይም የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተር ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ለማግኘት ሊኖር የሚችለዉ አነስተኛ የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽነሪ ዓይነት ብዛት ከ3 ማነስ የለበትም

ለ. የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽነሪዎች በማሰልጠኛ ተቋም ስም የተመዘገቡና የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት

ሐ. ቀደም ሲል በኪራይ መልክ ወደ ዘርፉ የገቡ የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽነሪ አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ይህ መመሪያ ከፀደቀ ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል

መ. የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽን ጥሩ የቴክኒክ ብቃት ላይ የሚገኝ እና የቴክኒክ ብቃቱ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ቦሎ) የተሰጠው፤

ሠ. በማሰልጠኛ ተቋም ስም ተመዝግበው የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት በላይ የሆኑ የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽነሪዎች አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ይህ መመሪያ ከፀደቀ ቀን ጀምሮ ለሁለት/2/ ዓመት ብቻ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ

ረ. የኤክስካቫተር፣ ሎደር፣ ዶዘር፣ ግሬደር፣ ክሬን፣ ሩሎ ኦፕሬተሮች ስልጠና አገልግሎት የሚሰጡ ማሽነሪዎች ጠቅላላ ክብደት ከ12ሺ. ኪ.ግ. በላይ

ሸ. የበክሁ ሎደር፣ ፎርክ ሊፍት፣ ትራክተር፣ እንዲሁም የኮምባይነር ኦፕሬተሮች ስልጠና አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎች ጠቅላላ ክብደት ከ6ሺ. ኪ.ግ በላይ መሆን አለበት

ሰ. ቀደም ሲል ወደ ዘርፉ የገቡ እና ጠቅላላ ክብደታቸዉ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሰዉ በታች የሆነ የተግባር ስልጠና መስጫ ማሽነሪዎች አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ይህ መመሪያ ከፀደቀ ቀን ጀምሮ ለአንድ(1) ዓመት ብቻ ይሆናል

## 5. <u>የአሰልጣኝ ማሽን ጥምርታ እና ሊኖር የሚችል የማስተማሪያ ክፍል ብዛት</u>

ተቋሙ ፈቃድ በጠየቀው /ባገኘዉ/ ማሽን ብዛት ጋር እኩል የሆነ የተግባር አሰልጣኝ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የንድፈ ሀሳብ አሰልጣኝ እና ሊኖር የሚገባ ማስተማሪያ ክፍል ብዛት ቀጥሎ

በተገለፀው ስንጠረዥ መሰረት ይሆናል። ነገር ግን የማሽን ዓይነት እና የማሽን ቁጥር በሚጨመርበት ወቅት የንድፍ ሀሳብ አሰልጣኝ እና የማስተማሪያ ክፍል ብዛትም በተመሳሳይ ቀመር የሚጨምር ይሆናል፡

| ተ.ቁ | የማሽን ዓይነት ብዛት | ሊኖር የሚችል የማሽን ብዛት | የሚያስፈልግ የአሰልጣኝ ብዛት | | ጠቅላላ የአሰልጣኝ ብዛት | የማስተማሪያ ክፍል ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የንድፈ ሀሳብ አሰልጣኝ | የተግባር አሰልጣኝ | | |
| 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 |
| | | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 |
| | | 3 | 1 | 3 | 4 | 1 |
| | | 4 | 2 | 4 | 6 | 2 |
| | | 5 | 3 | 5 | 8 | 3 |
| | | 6 | 3 | 6 | 9 | 3 |
| 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 |
| | | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 |
| | | 4 | 2 | 4 | 6 | 2 |
| | | 5 | 3 | 5 | 8 | 3 |
| | | 6 | 4 | 6 | 10 | 4 |
| 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 5 | 2 |
| | | 4 | 2 | 4 | 6 | 2 |
| | | 5 | 3 | 5 | 8 | 3 |
| | | 6 | 4 | 6 | 10 | 4 |
| 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 8 | 4 |
| | | 5 | 4 | 5 | 9 | 4 |
| | | 6 | 5 | 6 | 11 | 5 |
| 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 10 | 5 |
| | | 6 | 5 | 6 | 11 | 5 |



ሁን ኃ/ማርያም
ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

6. <u>የግንባታ እና የእርሻ መሳሪያዎች የኦፕሬተሮች ስልጠና መስጫ ማሽነሪዎች ደረጃ (ስታንዳርድ)</u>

እያንዳንዱ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ ኦፕሬተር ማስልጠኛ ተቋም በሚሰጠው የስልጠና ዓይነት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ስልጠና ለመስጠት በሚያስችል መልኩ በቂ የሆኑ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያዎች እንዲሁም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ከዚህ በታች በሰንጠረዡ በተመለከተው መሠረት እንዲኖሩት ያስፈልጋል

| ተ.ቁ | የግንባታ ወይም የእርሻ መሳሪያዎች እና የት/ት መርጃ መሳሪያ ዓይነት | የማስልጠኛ ማሽነሪ /መሳሪያ/ ደረጃ | የማሽን ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ባክሁሎደር፣ ፎርክሊፍት፣ ትራክተር፣ ኮምባይነር | ጠቅላላ ክብደቱ ከ6ሺ ኪ.ግ በላይ የሆነ | የስልጣኝና የማሽነሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| | እስካቫተር፣ ሎደር፣ ዶዘር፣ ግሬደር፣ ክሬን፣ ሩሎ | ጠቅላላ ክብደቱ ከ12ሺ ኪ.ግ በላይ የሆነ | የስልጣኝና የማሽነሪ ጥምርታን ባገናዘበ መልኩ |
| 2 | ኮምፒዩተር ከኤል ሲ.ዲ. ጋር | የሚሰራ | በአንድ ክፍል አንድ |
| 3 | ዴክና ቴሌቭዥን | የሚሰራ | በአንድ ክፍል አንድ |
| | የደህንነት ልብስ | ደረጀዉን የጠበቀ | ለናሙና ያህል ከሁሉም ቢያንስ ሶስት ሶስት |
| 4 | የእጅ ጓንት | | |
| 5 | የደህንነት ጫማ | | |
| 6 | ቱታ፣ | | |
| 7 | ቆብ (ሄልሜት) | | |

## 21. የሙያተኞች ተፈላጊ የትምህርት ሁኔታ

### 1. የተቋሙ ዳይሬክተር

ሀ. በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ወይም በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት

ለ. በትምህርት አመራር

ሐ. በቢዝነስ ማናጅመንት

መ. በአዉቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ

ሠ. በአዉቶሞቲብ ኢንጂነሪንግ ወይም

ረ. በሌሎች ተመሳሳይ የትምህርት ዘርፎች የመጀመሪይ ዲግሪ የተመረቀ ዜሮ ዓመት

ሸ. የሥራ ልምድ ወይም ዲፕሎማ ሆኖ ቢያንስ አግባብነት ያለው 2 ዓመት የሥራ ልምድ

### 2. የምዝገባና ገንዘብ ተቀባይ ሰራተኛ

ሀ. ሴክረታሪያል ሳይንስ

ለ. ኮምፒዩተር ሳይንስ

ሐ. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

መ. አካውንቲንግ

ከላይ በተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች 10+1 ሠርተፍኬት እና ከዚያ በላይ ዜሮ ዓመት የሥራ ልምድ ወይም 10ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀና የ1 ዓመት አግባብ ያለው የስራ ልምድ እና መሠረታዊ የኮምፒዩተር ዕውቀት ያለው

ከማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

3.የግንባታ እና የእርሻ መሳሪያ ዕጩ ኦፕሬተሮች አሰልጣኝ መስፈርት

በአውቶመካኒክ፣ አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ አውቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ፣ መካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ ወይም በአግሪካልቸራል መካናይዜሽን፣ ኢንጅን ሰርቪስ፤ ፓወር ትሬን ወይም አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ ማናጅመንት የትምህርት ዘርፍ ሆኖ፡-

ሀ. ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ዲፕሎማ፣ 12+2፣ 10+3፣ እና ደረጃ 3

ለ. ሁለት ዓመት አግባብነት ያለው የአሰልጣኝነት የስራ ልምድ ያለው

ሐ. በደረጃው የኮንስትራክሽን ማሽነሪን ወይም የእርሻ መሳሪያዎችን ኦፕሬተር የብቃት ማረጋጋጫ ፈቃድ ያለው

መ. በብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት (ሲኦሲ) የሚሰጥ የአሰልጣኝነት ብቃት ማረጋጫ ፈቃድ ያለው፤

ሠ. በባለስልጣን ወይም ዉክልና በተሰጠዉ አካል የተሰጠ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያዎች የአሰልጣኝነት ፈቃድ የወሰደ

22. **የማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ስለማደስና አድራሻ ስለመቀየር**

1. **ፈቃድ እድሳት**

ሀ. በተለያዩ ምክንያት በባለስልጣኑ ልዩ ዉሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር ለተቋማት የሚሰጠዉ ፈቃድ የሚያገለግለዉ በፈቃድ ላይ ለተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ብቻ ይሆናል

ለ. ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠዉ ተቋም የፈቃድ ጊዜው እንዳበቃ (እንደተጠናቀቀ) በአንድ (01) ወር ዉስጥ ቀርቦ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት

ሐ. ባለስልጣን መ/ቤቱ ወይም ዉክልና የተሰጠዉ አካል የእድሳት ጥያቄዉ ሲቀርብለት ተቋሙ በመስፈርቱ መሰረት አስፈላጊዉ ቅድመ ሁኔታ መሟላቱን አረጋግጦ በ10 ቀናት ዉስጥ ፈቃዱን ያድሳል

መ. ለማሰልጠኛ ተቋም የተሰጠዉን ፈቃድ ማሳደስ የሚቻለዉ በተቋሙ ባለቤት ወይም ህጋዊ ዉክልና በተሰጠዉ አካል በኩል ብቻ ይሆናል

ሠ. በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ዉስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ ተቋም በመመሪያዉ ላይ በተቀመጠዉ የቅጣት ደረጀ መሰረት እርምጃ ይወሰድበታል

2. <u>አድራሻ ስለመቀየር</u>

ሀ. ተቋማት ፈቃድ የተሰጣቸውን አድራሻ ሲቀይሩ በ10ቀን ዉስጥ ለሚመለከተው አካል በፅሁፍ ማሳወቅ አለባቸዉ.

ለ. ባለስልጣኑ ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በ15 ቀን ዉስጥ አዲሱ አድራሻ ተገቢውን መመዘኛ ያሟላ መሆኑን በባለሙያዎች አረጋግጦ አስፈላጊዉን የአድራሻ ማስተካከያ ያደርጋል

ሐ. የአድራሻ ለዉጥ ሲያደርግ ለባለስልጣኑ ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ያላሳወቀ ተቋም በዚህ በመመሪያ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ሥርዓት መሰረት ተጠያቂ ይሆናል

ማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

አዲስ አበባ

## ክፍል አምስት

## 23. የዲሲፕሊን እርምጃዎች

ሰንጠረዥ-01 ጥፋት ፈፅመዉ በተገኙት ማሠልጠኛ ተቋማት ላይ የሚወሰድ የዲሲኘሊን እርምጃ

| ቁ | የጥፋት ዓይነት | የሚወሰደው የዲሰፕሊን እርምጃ |
| --- | --- | --- |
| | ፈቃድ እንዲያገኝ ያስቻሉትን የመማር ማስተማር መስፈርቶችን ማለትም የመማሪያ ክፍሎች፣ ስልጠና መስጫ ማሽነሪዎች፣ አሠልጣኞች፣ የማስተማሪያ ማቴሪያሎች ወዘተ መካከል አንዱን እንኳን አንድሎ የተገኘ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በ15 ቀን ዉስጥ ማስተካከያ እዲያደርግ ይደረጋል፡፡<br>2. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ምንም ዓይነት ስልጠና እንዳይሰጥ ይታገዳል<br>3. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት ለ3 ወር የታገደ ከሆነ ለሦስተኛ ጊዜ ጥፋት የሥራ ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዝ ይደረጋል |
| | • በስልጠና መስጫ ስርዓተ ትምህርት መሰረት ስልጠና የማይሰጥ ወይም<br>• ባዘጋጀው የስልጠና መርሀ ግብር መሰረት የማያሰለጥን | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በ15 ቀን ውስጥ አስተካክሎ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እንዲያደርግ ይደረጋል<br>2. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ስልጠና እንዳይሰጥ ይታገዳል<br>3. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት ተቋሙ ለ3 ወር የታገደ ከሆነ ለ3 ጊዜ የሥራ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ይታገዳል |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | • ስስልጠና የሚጠየቁ መስፈርቶች እድሜ፣ የጤና ሁኔታ የትምህርት ደረጃ...ወዘተ የማያሟሉ ሰልጣኞችን ተቀብሎ ሲያሰለጥን የተገኘ ወይም<br>• 85% ከዚያ በላይ የስልጠና ሰዓት ያልተከታተለ ሰልጣኝን ለፈተና ያቀረበ ወይም<br>• ሰልጣኞች የሚያቀርቡትን ማስረጃ ትክክለኛነት ሳያጣራ ሥልጠና የጀመረ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ለ3 ወር ይታገዳል። ሰልጣኙም ከስልጥና ይታገዳል፣ ሰልጣኙ የኦፕሬተርነት ፈቃድ ወስደው ከሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል<br>3. ለሦስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ወይም ሌላ አይነት ጥፋት አጥፍተው ከተገኘ የተቋሙ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል |
| 4 | • የሰልጣኞችን የምዝገባ ሰነዶች፣ አቴንዳንስና የስልጠና መከታተያ ቅጽ በአግባቡ አደራጅቶ ተግባራዊ ያላደረገ ወይም<br>• ሰልጣኞች ስልጠና የሚጀምሩበትንና የሚያጠናቅቁበትን የጊዜ ፕሮግራም አዘጋጅቶ በግልፅ በሚታይበት ቦታ ያልለጠፈ ወይም<br>• አሰልጣኞችን ወይም ሰልጣኞችን መታወቂያ ወይም ባጅ እንዲያደርጉ ያላደረገ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል<br>2. በሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር እንዳያሰለጥን ይታገዳል<br>3. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት ለሦስት ወር ስልጠና እንዳይሰጥ የታገደ ከሆነ ለሦስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ወይም ሌላ ዓይነት ጥፋት አጥፍቶ ከተገኘ ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል |

ስማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

| | | |
|---|---|---|
| 5 | አዲስ የሚቀበላቸውን ሰልጣኞች ዝርዝር ስልጠና ከመጀመሩ በፊት ፈቃድ ለሰጠው አካል ሪፖርት ያላደረገ ወይም በራሱ ያስፈተነ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ የተጀመረው ስልጠና እንዲቋረጥ ይደረጋል፣ የተጠናቀቀ ስልጠና ከሆነ ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል፡፡ ያስፈተነ ከሆነ የፈተና ውጤት ተቀባይነት አይኖረውም፣ በዚህም ምክንያት ሰልጣኞች ላይ ለሚደርሰዉ ማንኛዉም ችግር ማሰልጠኛ ተቋሙ ኃላፊነት ይወስዳል<br>2. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ስልጠና እንዳይሰጥ ይታገዳል<br>3. በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት ለሦስት ወር ታግዶ ከሆነ ለሦስተኛ ጊዜ ጥፋት ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ |
| 6 | ፈቃድ ከተሰጠው ምድብ ውጭ ምዝገባ ወይም ስልጣና በመስጠት ወይም ለህብረተሰቡ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ዜጎች ላይ የማታለል ተግባር የፈፀመ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ያጠፋ ለ3 ወር ስልጠና እንዳይሰጥ ይታገዳል<br>3. በሶስተኛ ጊዜ ጥፋት የተቋሙ ፈቃድ ይሰርዛል |
| 7 | • በመመሪያው የተቀመጠውን የማሽንና የሰልጣኝ ጥምርታ በላይ ተቀብሎ ሲያሰለጥን የተገኘ ወይም<br>• አንድ ሰልጣኝ መሰልጠን ያለበትን ሰዓት ሙሉ ያላሰለጠነ | 1. ለመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል<br>2. ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ ለ3 ወር እንዳያሰለጥን ይታገዳል<br>3. በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት ለ3 ወር የታገደ ተቋም ከሆነ ለሦስተኛ ጊዜ ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ ፈቃዱ ይሰረዛል |

| | |
|---|---|
| ከባለስልጣን መ/ቤቱ ወይም ዉክልና ከተሰጠዉ አካል ህጋዊ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳያገኝ ፈቃድ ከተሰጠው ቦታውጭ ስልጠና የሰጠ | • ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የጀመረው ስልጠና እንዲያቋርጥ ተደርጎ የተቋሙ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡ ለፈጸመው ድርጊትና በዜጎች ላይ ለሚደርሰው አላስፈላጊ የጊዜ፣የገንዘብ ወጪዎች ተጠያቂ ይሆናል |
| የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ በተሰጠዉ ጊዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱን ያላሳደሰ | 1. እንዲያሳድስ የተሰጠዉን የጊዜ ገደብ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ዉስጥ ካቀረበ ከማስጠንቀቅያ ጋር ብር 3000 ተቀጥቶ ይታደሳል<br>2. በቅጣት የሚያድስበት ጊዜ ገደብ ካበቃ ለተቋሙ ማሳወቅ ሳያስፈልግ ፈቃዱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል |
| ተገምግሞ ፈቃድ የወሰደበትን አድራሻ ሲለዉጥ ለፈቃድ ሰጪ አካል ያላሳወቀ | 1. ማሳወቅ ያለበት ጊዜ አብቅቶ በ1 ወር ውስጥ ካሳወቀ ከማስጠንቀቂያ ጋር ብር 5000 ተቀጥቶ አዲሱ አድራሻ በባለሙያ እንዲገመገም ይደረጋል<br>2. ማሳወቅ ባለበት ጊዜ ውስጥ ሳያሳውቅ ከአንድ ወር በላይ ከሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል |
| ሳልታደሰ የቤት ኪራይ ውል ወይም የተግባር ስልጠና ቦታ የኪራይ ዉል ሲሰራ የተገኘ | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በ15 ቀናት ውስጥ ዉሉን እንዲያድስ ይደረጋል፡፡ በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ዉሉን ካለሳደሰ ምንም ዓይነት እንዳያገኝ ይደረጋል<br>2. ቀደም ሲል በተመሳሳይ ወይም በሌላ ዓይነት ጥፋት የፅሁፍ ማጠንቀቂያ ካለው ለሁለተኛ ጊዜ ለ3 ወር ምንም ዓይነት ስልጠና እንዳይሰጥ ይደረጋል<br>3. በማንኛውም ዓይነት ጥፋት ለ3 ወር የታገደ ከሆነ ለ3ኛ ጊዜ |



ከግሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

| | | |
|---|---|---|
| | | ጥፋት ፈፅሞ ሲገኝ የተቋሙ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ይሰረዛል |
| 12 | አሰልጣኝ ወይም ማሽን በአካል ሳይኖር የራሱ ማሽን ወይም አሰልጣኝ ያለው በማስመሰል ዶክመንቶችን በማቅረብ ፈቃድ ወስዶ የተገኘ ተቋም | 1. ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማጠንቀቂያ ተሰጥቶት በአንድ ወር ውስጥ እንዲያሟላ ይደረጋል<br>2. በማንኛውም ዓይነት ጥፋት የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠ ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ለ3 ወር ከስልጠና እንዲታገድ ይደረጋል<br>3. በማንኛውም ዓይነት ጥፋት ለ3 ወር የታገደ ተቋም ከሆነ ለ3ኛ ጊዜ ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል |

13. ሌላ ሰው ፈተና እንዲፈተንለት ያደረገ ሰልጣኝ የዕለቱ የተፈታኙ ፈተና ተሰርዞ ከተያዘበት ዕለት ጀምሮ ለአንድ አመት ከስልጠና ይታገዳል፤ በወቅቱ ሲፈተን የተገኘዉም ጥፈተኛ ተፈታኝ በህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል

14. የተጭበረበረ ወይም አስመስሎ የተዘጋጀ መረጃ የሚያቀርብ ሰልጣኝ ጉዳዩ በታወቀበት ጊዜ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም የእርሻ መሳሪያ የኦፕሬተርነት ስልጠና እንዲያቋርጥ ወይም የወሰደው ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰርዞ ለሰራው ወንጀል በህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል።

ካሣሁን ገ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## 24. የዲሲፕሊን ቅጣት የቆይታ ጊዜ

በዲሲፕሊን ግድፈት ምክንያት በማሰልጠኛ ተቋማት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች የቆይታ ጊዜ ገደብ እንደየ ጥፋቱ ክብደት መጠን እና ዓይነት የሚለያይ ሲሆን በአጠቃላይ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

1. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የቆይታ ጊዜ ማስጠንቀቂያዉ በፅሁፍ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለ1 ዓመት ይሆናል
2. የ3 ወር የዕገዳ ቅጣት የቆይታ ጊዜ ዕገዳው በፅሁፍ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለ18 ወር የሚፀና ይሆናል
3. ፈቃዱ የተሰረዘበት ማሰልጠኛ ተቋም ወደ ዘርፉ ዳግመኛ መመለስ የሚችለው ፈቃዱ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ(1) ዓመት በኋላ እንዳ አዲስ ተገምግሞ የተቀመጠዉን መስፈርት አሟልተዉ ሲገኝ ይሆናል፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25. ክልከላ

1. ይህ መመሪያ ከፀደቀ ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኂላ በኪራይ ስም ወይም በማሰልጠኛ ተቋም ባለቤት ስም በተመዘገቡ ማሽነሪ ስልጠና መስጠት አይቻልም
2. የንድፈ ሀሳብ ወይም የተግባር አሰልጣኞች ስልጠና መስጠት የሚችሉት በቋሚነት በተቀጠሩበት ማሰልጠኛ ተቋም ብቻ ሲሆን በተለያዩ ተቋማት ወይም ቅርንጫፍ ተቋም ተዘዋውሮ ማሰልጠን የተከለከለ ነው
3. በፈተና ወቅት መኮራረጅ የተከለከለ ነው፡፡ ሲኮርጅ የተገኘ ሰልጣኝ ውጤቱ ይሰረዛል

### 26. መመሪያውን ስለማስፈፀምና የመተባበር ግዴታ

1. የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማእከላት /C.O.C/ እንዲሁም በትራንስፖርት ባለስልጣን ውክልና የተሰጣቸው መንግስታዊ አካላት ይህንን መመሪያ ተቀናጅተው ያስፈፅማሉ
2. ማንኛውም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ እና የእርሻ መሳሪያ ኦፐሬተሮች ማሰልጠኛ ተቋም ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት

### 27. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

1. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም
2. የከበድ ኮንስትራክሽን ማሽነሪ እና የእርሻ መሣሪያ ኦፐሬተሮች ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰራር መመሪያ ቁጥር 01/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሮዋል



ጥላሁን ገ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

## 28. መመሪያውን ስለማሻሻል

- ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል

## 29. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

- ይህ መመሪያከሚያዝያ 10 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል

ካሣሁን ኃ/ማርያም

የትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር

ሚያዝያ 2010 ዓ.ም.